# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

*ተዛማጅ ሠነዶች፡-* ACA, ACG-RA, ACG-RB, ACF, ACF-RA, ACI, ACI-RA, GKA-RA, GMA, JFA, JFA-RA, KLA, KLA-RA

*ኃላፊነት ያላቸው ቢሮዎች፡-*ዋና ኦፐሬቲንግ ኦፊሰር፣ የሰብአዊ አገልግሎት ልማት ኃላፊ፣ የዲስትሪክት ኦፐሬሽንስ ኃላፊ፣ የአካዳሚክስ ዋና ኃላፊ/Chief Operating Officer; Chief of Human Resources and Development; Chief of District Operations; Chief Academic Officer

## አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊ፣ የባህል ብቃት

**I. ዓላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA አፈፃፀም ኃላፊነት የሚወስዱ አግባብ ያላቸው የአመራር ቢሮዎችን ለመሰየም፣ አድሎዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊ የባህል ብቃት፣ እና ሁሉም የፌዴራል፣ የስቴት እና የአካባቢ ህጎች ከአድሎ ነፃ በሆነ ፍትኃዊነት መተግበራቸውን እና መከበራቸውን ማረጋገጥ።

ስለ አድልዎአዊነት ቅሬታ/ክስ ምላሽ የመስጠት ሂደቶችን ለመመሥረት፥

**II. ትርጉም**

A. በስራ ላይ የሚፈፀም አድልዎ 1964 የዜጎች መብት ህግን "Title VII" በመጣስ በተለይ ኢፍትሃዊ ተግባር የሚፈፀም ሲሆን፤ ይኼውም በአንድ ሰው ላይ ዘር፣ ቀለም፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ጾታ (እርግዝናን፣ የፆታ ማንነት፣ ጾታዊ ዝንባሌን ጨምሮ) ወይም ሀይማኖት፣ ወይም ሌሎች ተገማች ባህርይን ምክንያት በማድረግ የሚፈፀም አድሎአዊነት፤ በቦርድ ፖሊሲ ACA ላይ፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት እንደተገለጸው እነዚህን ምክንያት አድርጎ የማግለል አድሎአዊ ተግባር መፈፀም ህገ-ወጥ ያደርገዋል።

B. የሚመለከተው አካል ማለት ቅሬታ አቅራቢው(ዋ) ሰው ወይም ሰዎች፣ እርምጃ እንዲወሰድ ጥያቄ/አቤቱታ የሚቀርብለ(ላ)ት ማንኛውም ሰው ወይም ቅሬታውን ለመፍታት እርምጃ የሚወሰድበ(ባ)ት ሰው/ሰዎች ማለት ነው።

**III. ጉዳዩ**

የቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊ፣ እና የባህል ብቃት፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች የሚጠበቅባቸውን ከፍተኛ የትምህርት እና የሥራ አፈጻጸም ባህል እንዲያዳብሩ እና እንዲያሳድጉ ቦርዱ ያለውን እምነት ይገልጻል። በፍትሃዊነትና፣በእኩልነት ላይ የተመሠረተ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ብዝሃነትን አካታች የሆኑ የስራ እና የትምህርት አካባቢዎችን በመጠበቅ፤ የእድሎችን የተዛባ፣ አድሎአዊ፣ ኢፍትሃዊ አተገባበር ማስወገድ፣ የሁሉንም ተማሪዎች የውጤት ደረጃቸውን ያሳድጋል፣ እና በትምህርት ስኬታማነት ላይ የሚታዩትን የውጤት ክፍተቶች በከፍተኛ ሁኔታ ይፈታል/ያሻሽላል።

በፖሊሲ ACA ላይ እንደተገለጸው በአንድ ሰው ላይ “ተገማች ባህርያት” ላይ የተመሰረተ መድልዎ ተቀባይነት የለውም። MCPS ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች እና ለቤተሰቦች ያለውን ሀላፊነት ለመወጣት እና የማህበረሰቡን የረዥም ጊዜ ጥረት ፍትሃዊነትን፣ አካታችነትን እና ሁሉም ሰው ተቀባይነት ያለው መሆኑን ፍትኃዊ አመለካከት ለመፍጠር፣ ለማዳበር እና ለማስተዋወቅ የሚያደርገውን ጥረት እንዲያሳካ እንቅፋት ይሆናል።

## IV. ቅደም-ተከተል/ሂደቶች

### A. የአድሎዊ አፈጻፀም ቅሬታ

1. MCPS ሁሉንም ሪፖርት የተደረገ የአድሎአዊነት ቅሬታዎችን ገምግሞ ምርመራ ማድረግ እና የድጋፍ እርምጃዎችን መስጠትን ጨምሮ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል።

2. MCPS የሰራተኞች እና የሚመለከታቸው የሶስተኛ ወገን ጥያቄዎችን ጨምሮ የምርመራዎችን ምስጢራዊነት በሚመለከታቸው ህጎች ተንተርሶ MCPS እንደዚህ ያሉ ቅሬታዎችን የመመርመር እና የመፍታት ሃላፊነት ይጠበቃል።

3. ግለሰቡ በቅን ልቦና የመድልዎ ቅሬታ ያቀርባል ወይም ይሳተፋል ወይም ስለ አድልዎ ቅሬታ ምርመራ ይተባበራል በሚል ሰበብ/ምክንያት በማንኛውም ግለሰብ ላይ ምንም ዓይነት አሉታዊ እርምጃ አይወሰድም።

### B. በተማሪዎች በኩል ለሚፈፀም መድልዎ ከተማሪዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎች

1. የዲስትሪክት ኦፕሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ፣ የተማሪ ደህንነትና ስርአት የማስከበር አገልግሎት ክፍል፤ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከፌዴራል፣ከስቴት እና ከአካባቢ ህጎች ጋር በማጣለጥ ለተማሪዎች አድልዎ የሌለበት ፍትሃዊ አገልግሎት ለመስጠት ቦርዱ ያለውን ቁርጠኝነት ተግባራዊ የማድረግ [1] ሃላፊነት አለበት።

2. በቦርድ ፖሊሲ JHF ላይ እንደተቀመጠው፡ ጉልበተኝነት፣ትንኮሳ፣ወይም ማስፈራራት በተማሪዎች ላይ የሚደረግ መድልዎ ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራትን ሊያካትት ይችላል። MCPS የጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም የማስፈራሪት ድርጊቶችን ሪፖርት የማድረግ ሂደቶች MCPS ደንብ JHF-RA፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት በሚለው ላይ ተገልፀዋል።

3. በቦርድ ፖሊሲ ACF ላይ እንደተገለጸው፣ የተማሪዎች የፆታ ብልግና እና ጾታዊ ትንኮሳ፣ በተማሪዎች ላይ የሚፈጸም መድልዎ ወሲባዊ ትንኮሳ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። MCPS የወሲብ ትንኮሳ ድርጊቶችን ሪፖርት የማድረግ ሂደቶች JHF-RA፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት በሚለው ላይ ተቀምጠዋል።

4. ከላይ በሌላ መልኩ ያልተገለጹ ተማሪዎችን በተመለከተ የሚነሱ የአድሎአዊነት ስጋቶች ወይም ቅሬታዎች በቦርድ ፖሊሲ KLA፣ከህዝብ ለሚነሱ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት፣እና MCPS ደንብ KLA-RA፣ስጋቶች፣ ቅሬታዎች፣ እና ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይግባኝ ማቅረብ።

5. የሜሪላንድ ህግ የተብራራ ኮድ፣የትምህርት አንቀጽ §26-704 በመጣስ የተፈፀመ አድሎአዊነት፣ በሜሪላንድ ደንብ §13A.01.07 መሠረት የአድሎአዊነት ቅሬታ ለሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በጽሁፍ መቅረብ ይችላል

6. በማንኛውም ጊዜ፣ Title VI ወይም Title IX ተጥሷል የሚል ተማሪ US.S. Department of Education's Office for Civil Rights (OCR) ቅሬታ ማቅረብ ይችላል/ትችላለች። አንድ ተማሪ

[1] ከማርች 2, 2023 ጀምሮ፣ የዲስትሪክት ኦፕሬሽን፣ የተማሪ ደህንነት ጥበቃ ክፍል ጽ/ቤት የጥላቻና-አድሎአዊነት ክስተቶችን ቅሬታ በተመለከተ የአፈጻፀም መመሪያ ሰጥቷል። እንደነዚህ ያሉ ቅሬታዎች MCPS ቅጽ 226-5፣ የጥላቻ-ዝንባሌና ክስተት ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ በመጠቀም ሪፖርት መደረግ አለባቸው። የተሞላው ቅጽ ለተጎጂው(ዋ) ተማሪ ትምህርት ቤት ርእሰመምህር ይሰጣል።

ወደ OCR ቅሬታ ከማቅረቡ(ቧ) በፊት ወይም በኋላ ወደ MCPS ቅሬታ ማቅረብ አይጠበቅበ(ባ)ትም።

U.S. Department of Education, Office of Civil Rights ዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የሲቪል መብቶች ቢሮ
OCR ኤሌክትሮኒክ የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ
(http://www.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html)፣ወይም

U.S. Department of Education, Office for Civil Rights
Lyndon Baines Johnson Department of Education Building
400 Maryland Avenue, SW
Washington, DC 20202-1100

C. የሥራ ቅጥር መድልዎ ቅሬታ

1. የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት "Office of Human Resources and Development (OHRD)" በስራ ቦታ አድልዎ እንዳይደረግ ቦርዱ ያለውን ቁርጠኝነት ተግባራዊ ለማድረግ እና በሥራ ቦታ አድሎአዊ ያልሆኑ ህጎችን በሚመለከት MCPS የሚመለከታቸውን የፌዴራል፣ የስቴት እና የአካባቢ ህጎች እንዲከበሩና ተግባራዊ እንዲደረጉ የማስተባበር ሃላፊነት አለበት። የሰራተኞች መድልዎ ቅሬታዎች/ክሶች ሲቀርቡ በፌዴራል እና የስቴት ህግ መስፈርቶች ላይ በመመርኮዝ በሰብአዊ የሥራ ግብረኃይል ስነ ስርአት አስከባሪ ክፍል በቅሬታ ሰሚና ምርመራ ዲፓርትመንት (DCI) አማካይነት ምርመራ ይካሄዳል።

2. ማንኛውም ሰው የቅጥር አድልኦ ተፈጽሞብኛል ብሎ ሲያመለክት ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ እንዲህ አይነት አድሎአዊ ድርጊት ሲፈጽም ከተመለከተ(ች) ክስተቱን በፍጥነት ወደ DCI ሪፖርት ማድረግ አለበ(ባ)ት። (ተማሪዎችን በሚመለከት የአድልዎ አሠራርን ሪፖርት የማድረግ ሂደቶች ከዚህ በታች section III.C ላይ ተብራርቷል።)

   a) በስራ አቀጣጠር መድልዎ ተፈፅሞብኛል የሚል የግለሰብ ቅሬታ/ክስ ማቅረቢያ ቅፅ 230-39፣ የአድሎአዊ አፈጻፀም ቅሬታ ወይም የስራ ቦታ ጥቃት የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ በመሙላት በኢሜል DCI@mcpsmd.org በቀጥታ እንዲደርስ መደረግ አለበ(ባ)ት። በአማራጭ፣ ሰራተኞች እንደአስፈላጊነቱ ጉዳዩን ወደ DCI እንዲመራ ርዕሰ መምህራቸውን/ተቆጣጣሪቸውን ማነጋገር ይችላሉ።

   b) ቅሬታ አቅራቢው(ዋ) ቅፅ 230-39፣ የመድልዎ ቅሬታ ወይም ስለ ስራ ቦታ ጉልበተኝነት ቅጽ ካልሞላ(ች)፣ DCI የሰው ሃይል ስነ ስርአት አስከባሪ ኦፊሰር DCI ምርመራ ከመጀመሩ በፊት ከቅሬታ አቅራቢው(ዋ) ጋር በመነጋገር ቅጹ እንዲሞላ ያደርጋል/ታደርጋለች።

3. ምርመራ

   a) የተጠረጠረው ድርጊት የሥራ ቅጥር መድሎ መሆኑን በሚወስንበት ጊዜ ስለ ክስተቱ የተነዘበ መረጃ እና ስለ ጉዳዩ አጠቃላይ ሁኔታ፣ ቅሬታ የቀረበበት ክስተት ሁኔታ ጭምር ግምት ውስጥ ይገባል።

   b) በሁሉም ደረጃ ማንኛውም የሚመለከተው አካል በማናቸውም የመረጠ(ች)ው ግለሰብ

ሊደገፍ ይችላል።[2]

c) 60 የስራ ቀናት ውስጥ የሰው ሃይል ስርአት አስከባሪ መኮንን የሚከተሉትን ያደርጋል፦

(1) ቅሬታው በዚህ ደንብ መሠረት ለመታየት የሚችል አግባብነት ያለው መሆኑን ከተገመገመ በኋላ አግባብነት ካለው፥

(2) የቀረበውን ክስ/ቅሬታ መርምር፣ ውሳኔ መስጠት እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ወገኖችን ማሳወቅ።

d) ጉዳዩን በሚገመግሙበት ወቅት፣ ቅሬታው የምርመራውን መስፈርት ካላሟላ በአቤቱታው ውስጥ ለተጠቀሱት ሌሎች ወገኖች ማሳወቅ ሳያስፈልግ ጉዳዩ ወደ ቅሬታ አቅራቢው(ዋ) ይመለሳል።

e) የተራዘመውን የጊዜ ገደብ እና ምክንያት ለሚመለከታቸው ሁሉ ወዲያውኑ እንዲያውቁት ከተደረገ የሰው ሃይል ስር ስርአት አስከባሪ ባለስልጣን አስገዳጅ በሆኑ ምክንያቶች የጊዜ ገደቡን ሊያራዝም ይችላል።

4. ሰራተኛ ስለ አድልዊ ውሳኔ ይግባኝ ማለት

a) የሰው ሃይል ስነ ስርአት አስከባሪ የሰጠው ውሳኔ ለዋና ኦፐሬሽን ኦፊሰር (COO) ይግባኝ ሊባል ይችላል።

b) አቤቱታ አቅራቢው(ዋ) ውሳኔው በቀረበ 10 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማቅረብ አለበ(ባ)ት።

c) ከአቤቱታ አቅራቢው(ዋ) በጽሁፍ የቀረቡ የምርመራ ሰነዶችን እና ክርክሮችን ለመገምገም የሰለጠነ አጣሪ ባለሙያ ይመደባል።

d) ቅሬታው በጽሁፍ በደረሰው 10 ቀናት ውስጥ፣ COO የማጣራት ኃላፊነት የሚመለከተው አካል ማድረግ ያለበ(ባ)ት —

(1) ከአቤቱታ አቅራቢው(ዋ) በጽሁፍ የቀረቡ የምርመራ ሰነዶችን እና ክርክሮችን መገምገም፣

(2) በችሎቱ ኃላፊ ውሳኔ የቀረበውን መረጃ ለማብራራት ከቅሬታ አቅራቢው(ዋ) ጋር ስብሰባ ቀጠሮ መያዝ፣

(3) የይግባኙን ውጤት እና የውጤቱን ምክንያት የሚገልጽ የጽሁፍ ውሳኔ መስጠት፣ እና

(4) 30 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለቦርዱ ይግባኝ ለማለት ለቅሬታ አቅራቢው(ዋ) እና በቦርድ ፖሊሲ BLB፣ የይግባኝ ችሎትን የሚመለከቱ የአሰራር ደንቦች እና በስቴት ህግ መሠረት ያላቸውን መብት ማሳወቅ ይጠበቅበ(ባ)ታል።

---

[2] ከሰራተኛው(ዋ) ጋር አብሮ እንዲሆን/እንድትሆን "የሚመርጡ(ጧ)ት ሌላ ግለሰብ" የሠራተኞች የጋራ ድርድር አስፈጻሚ ክፍል ተወካይን ያካትታል።

5. የሥራ ቅጥር መድልዎ ቅሬታዎች/ክሶች MCPS ደንብ GKA-RA፣ አስተዳደራዊ ቅሬታ ውስጥ የተገለጸውን የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሂደት አይመለከትም።

6. በዚህ ደንብ ውስጥ በተገለጸው መሰረት የሥራ ቅጥር አድልዎ ቅሬታን መከታተል ቅሬታ አቅራቢው(ዋ) የሜሪላንድ የሲቪል መብቶች ኮሚሽን (MCCR) ቅሬታ በቀጥታ mccr.maryland.gov ወይም ስለ እኩል የስራ እድል ኮሚሽን (EEOC) ቅሬታ በቀጥታ EEOC፣ ባልቲሞር የዲስትሪክት ጽሕፈት ቤት ቅሬታ/ክስ ከማቅረብ አይከለክልም ወይም አያግድም።

   a) U.S. Equal Employment Opportunity Commission
   Baltimore Field Office
   GH Fallon Federal Building
   31 Hopkins Plaza, Suite 1432
   Baltimore, MD 21201
   1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY)

   b) በተሻሻለው 1972 የትምህርት ህግ ማሻሻያ ድንጋጌ መሠረት በዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት መምሪያ Title IX የሰራተኛ ቅሬታ ለሲቪል መብቶች ፅህፈት ቤት ሊቀርብ ይችላል።

7. የዲሲፕሊን እርምጃ

   ሰራተኞች አድልዎ ሲፈጽሙ፣ በቀል ወይም የበቀል እርምጃ ሲወስዱ እና/ወይም ሆን ብለው የሐሰት ውንጀላ የሚፈፅሙ ሰራተኞች ላይ የሚያስከትለው መዘዝ የድስፕሊን ቅጣት እርምጃ ይወሰድባቸዋል። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በጽሑፍ ተግሣጽ፣ ሙያዊ ምክር፣ የሥራ መመደብ ለውጥ ማድረግ፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግ፣ ከሥራ መታገድ፣ ወይም ሥራ ማቋረጥን ሊያስከትል ይችላል ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም።

C. MCPS ውስጥ ያሉ ስጋቶችን ወይም የአድሎአዊ አሠራር ቅሬታዎችን የሚያመጡ የማህበረሰብ አባላት በቦርድ ፖሊሲ KLA እንደተገለጸው ወደ መደበኛ የአቤቱታ ሂደት መምራት አለባቸው፣ ከህዝብ ለሚመጡ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት፣ እና MCPS ደንብ KLA-RA፣ ከህዝብ ለሚነሱ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት።

## V. *ግንኙነት፣ ሪፖርት ማድረግ እና ሙያዊ ትምህርት*

A. የፀረ መድሎ መግለጫ

1. MCPS ፀረ መድሎ መግለጫ ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ የቦርዱን አቋም ያንፀባርቃል፤ እንዲሁም የስቴት እና የፌደራል መስፈርቶችን ያከብራል።

   የሜሪላንድ ደንቦች የፀረ መድልዎ መግለጫው የሚከተሉትን እንዲያካትት ይጠይቃሉ፦

   በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት “ሁሉም የሕዝብ ት/ቤቶች እና በሕዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር እንዲሰሩ ይጠበቅባቸዋል፦

   a) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ ታይትል VI፣ እና

   b) የሜሪላንድ ህግ ኮድ የትምህርት አንቀፅ ታይትል 26፣ ንዑስ አንቀጽ 7፣ የህዝብ ት/ቤቶች

እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች –

(1) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በትውልድ ቦታ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ዝንባሌ፣ በፆታ ማንነት፣ የአሁን ተማሪን፣ የወደፊት ተማሪን፣ ወይም የአሁኑን ወይም የወደፊት ተማሪን ወላጅ ወይም አሳዳጊ የአካል ጉዳተኝነት ያላቸው ተማሪዎች ላይ አድልዎ ማድረግ ክልክል ነው፣

(2) የወደፊት ተማሪን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁን ተማሪ ማባረር ወይም ከአሁን ተማሪ፣ የወደፊት ተማሪ፣ ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪ ወላጅ ወይም አሳዳጊ በግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ሀይማኖት፣ ጾታ፣ ዕድሜን፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የጾታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳትን ምክንያት አድርጎ ት/ቤት እንዳይመዘገቡ መከልከል፣ ወይም

(3) የቅሬታ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎ ፈፅመዋል በሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም የተማሪው(ዋ) አሳዳጊ ላይ ቅጣት መፈፀም ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ።"

2. MCPS ፀረ መድልዎ መግለጫ MCPS ድረ ገጽ ላይ በጉልህ ተቀምጧል።

3. MCPS ፀረ መድልዎ መግለጫ ሶስት ወይም ከዚያ በላይ በሁሉም የህትመት ገፆች አርትኦት፣ ግራፊክስ እና በህትመት አገልግሎት ክፍል (EGPS) ከጁን 30, 2023 በኋላ በሚታተም ማንኛውም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስርዓት አቀፍ ሰነዶች ውስጥ ይካተታል።

4. የጀነራል ካውንስል ቢሮ/Office of the General Counsel (OGC) ከጁን 30, 2023 በኋላ የወጡ፣ የተሻሻሉ፣ ክለሳ የተደረገባቸው ወይም የተገመገሙትን MCPS አድልዎ የሌለበት መግለጫ በቦርድ ፖሊሲዎች እና MCPS ደንቦች ላይ የማካተት ሀላፊነት አለበት።

5. በ EGPS የታተሙ ሰነዶች ወይም በ OGC የታተሙ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች አሁን ባለው MCPS የፀረ መድልዎ መግለጫ እና የሰነድ ትርጉም ፕሮቶኮል ሲከለሱ፣ ሲሻሻሉ ወይም እንደገና ሲታተሙ ይሻሻላሉ።

B. የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ፖሊሲ ACA እና የፌደራል እና የስቴት አድሎአዊ ያልሆኑ ህጎች ትግበራ ግቦችን፣ አላማዎችን፣ ስልቶችን እና የጊዜ ሰሌዳዎችን ለማዘጋጀትና ለማሳካት መረጃዎችን የመተንተን ሂደት የማቋቋም ሃላፊነት አለበት።

1. የጋራ ተጠያቂነት መምሪያ፡- በቦርድ ፖሊሲ ACA፣ ፀረ መድሎ፣ ፍትሃዊነት እና ባህላዊ ብቃት ፖሊሲ ላይ የተገለጹትን በቁርጠኝነት ለማሳካት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ያሉትን ድንጋጌዎች የመተንተን እና ክፍተቶችን የመለየት ሃላፊነት አለበት።

2. በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ መረጃ መሰብሰብ፣ ሪፖርቶች ወይም የውስጥ ሰነዶችን በቦርድ ለመተንተን ከማንኛውም ዘርፍ በተለየ ሁኔታ እያንዳንዱን ዘር እና ጎሳ ቡድን የሚወክል ቢያንስ 5 በመቶ የሚሆነውን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከተመዘገቡት ተማሪዎች ማካተት አለበት።

ተዛማጅ ምንጮች፡- ዩ.ኤስ. ሕገ መንግሥት U.S.C.)1964 ማሻሻያ 14፣ የሲቪል መብቶች ህግ ታይትል VI, 42 U.S.C. § 2000d et seq.1964 የተሻሻለው የሲቪል መብቶች ህግ Title VII, 42 U.S.C. § 2000e et seq.Title

IX ስለ 1972 የትምህርት ማሻሻያ 20 U.S.C. § 1681 et seq.፣34 የፌደራል ደንብ ኮድ (CFR)፣ ክፍል 106, 34 CFR ክፍል 100፣ ስለ አካል ጉዳተኞች ትምህርት ህግ (IDEA)፣ 20 U.S.C. § § 1400-1487፣ 1973 የተሃድሶ ህግ የተሻሻለው ሰክሽን 504፣ 29 U.S.C. § 794፣ ስለ አካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን የወጣ ህግ (ADA)፣ 42 U.S.C. § 12131 et seq.፣1866 የሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ 1981፣ 42 U.S.C. § 1981፣ 1967 በሥራ ስምሪት ሕግ ስለ ዕድሜ መድልዎ፣ 29 U.S.C. §§ 621-634፣ 1963 ስለ እኩል ክፍያ ህግ፣ 29 U.S.C. § 206 (d)፣ በሜሪላንድ ሕገ መንግሥት ስለ ህሙማን ጥበቃና ተመጣጣኝ እንክብካቤ እኩል መብት ማሻሻያ ሕግ፣ 42 U.S.C. § 18001 et seq. ፣ የሜሪላንድ ሕገ መንግሥት የመብቶች መግለጫ (አንቀጽ 46)፣ የተብራራ የሜሪላንድ ህግ ኮድ፣ የስቴት መንግስት አንቀፅ፣ ታይትል 20፣ ሰብአዊ ግንኙነት፣ የተብራራ የሜሪላንድ ህግ ኮድ፣ የትምህርት አንቀጽ §4-141፣ §6-104፣ እና §7-424.1፣ የሜሪላንድ ደንብ ኮድ (COMAR) §13A.05.01፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የዘር ፍትሃዊነት እና ማህበራዊ ፍትህ ህግ ማሻሻያ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ኮድ §1A-201፣ §2-64A፣ §2-81C፣ §27-83 እና §33A-14፣ MCPS የመከባበር ባህል ኮምፓክት[3]፣MCPS የተማሪ ስነምግባር ህግ፣ MCPS የሰራተኛ ስነምግባር ህግ፣ የሀይማኖት ልዩነትን ስለማክበር MCPS መመሪያዎች/ደንቦች፣ MCPS ስለ ተማሪ ጾታ ማንነት መመሪያዎች።

**የደንቡ ታሪክ፦** አዲስ ደንብ ጁላይ 5, 2005፤ ፌብሩዋሪ 21 ቀን 2023 ተሻሽሏል፤ COMAR 13A01.07፣ ኤፕሪል 19, 2024 ቴክኒካዊ ማሻሻያ ተደርጎበታል።

[3] የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ፣የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት አሶስዬሽን፣ የአገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች አለም አቀፍ ማህበር ሎካል/Service Employees International Union Local 500 እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የአስተዳዳሪዎች እና የርእሰመምህራን ማህበር መካከል የሚከናወን የመከባበር ባህል

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መግለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው:-
  (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
  (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች:-
    (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
    (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
    (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

<table>
<tr><td>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:-***</td><td>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:-***</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>1973 የተሃድሶ ድጅንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:-</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:-</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 | 504@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:-***</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተዛለጠ ነው።

**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተዛለጠ ነው።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል:-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር:- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, ዐወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024